## የቃናዋ እመቤት

ወይን ጠጁ ሲያልቅባቸው፣
የሚያደርጉት ሲጠፋቸው፣
መች ዝም አለች እናታቸው፣
እመብርሃን መውጫቸው።
  የዶኪማስ ባለውለታ፣
  የአገልጋዮቹ ትዝታ፣
  የእድምተኞቹ ሁሉ እርካታ፣
  የሐዋርያት አለኝታ።
የምልክቶች መጀመሪያ፣
ሲያደርጋት ልጇ አክብሮ፣
ለኛ እንድትሆን እዘክሮ፣
ሲለምነን በሳ ላይ አድሮ፣
ፈጥኖ ሰማት በአንክሮ።
  የቃናዋ እመቤት አማላጅዋ፣
  የማይቋረጠው እርዳታዋ፣
  የማይቆጠረው ስጦታዋ፣
  የማይለካው ዋጋዋ፣
  ልጆቼ ትለናለች፣
  በፍቅሯ እየሳበች፣
  በክንዷ እያቀፈች፣
ልታወጣን ከዓለም፣
ወድቀን እንዳንሰጥም፣
ልትመራን ደግፋ፣
ልትሆነን የኛ ተስፋ፣
ልትታደገን እንዳንጠፋ፣
  ከተፍ አለች ፈጥና፣
  መላእክተ ብርሃንን አስከትላ፣
  እየመራች ልታደርሰን፣
  የገነትን ደጃፍ ልታሳየን፣
  አይ እመቤቴ እሩኅሩኋ፣
  መቼ ያልቃል ደግነቷ፣
  ይፈውሳል መድሐኒቷ፣
  ለአመነባት በአማላጅነትዋ።
ተራው ውኃ ተለውጦ፣
ስም ተሰጥቶት ፀበል ተብሎ፣
እውሩን እያበራ፣
ጎባጣውን እያቀና፣
አንካሳውን እያረታ፣
ለምጻሙን እያነጻ፣
ዲያብሎስን እየቀጣ፣
መግቢያ መውጫ እያሳጣ፣
የቃናው ውኃ ዛሬም አለ፣
የድንግልን ትዕዛዝ እየተቀበለ፣
እስከ ምፅዐት ሳይቋረጥ፣
ድህነት ፈውስን ለኛ ሲሰጥ።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ።
ለንደን
ጥር 1997